የሰ/መ/ቁ. 196128
ቀን ፡- ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ መቅደስ ወልደማርያም ፡- ጠበቃ ነብዩ ምክሩ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ታምሩ በቀለ፡- ጠበቃ ዘውዱነህ ዘኪዮስ ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች ተቃዋሚ ሲሆኑ ተጠሪ የስር አፈጻጸም ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ከወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው እና ኤድሰን ካርጎ ኃ/የተ/የግል ማሕበር ጋር ተከራክረው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ ምክንያት ውሳኔውን ለማስፈጸም የአፈጻጸም ክስ አቅርበዋል፡፡ ለፍርዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 1137 የሆነ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው ንብረት ነው በማለት ለእዳው መክፈያ እንዲሆን ጠይቀው አፈጻጸም ችሎቱ ንብረቱ እንዲከበር ያደረገ ሲሆን አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ንብረቱ እንዲለቀቅ የተቃውሞ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአፈጻጸም የተከበረው ንብረት የሚች ወንድይፍራው መንገሻና የእኔ ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት ነው፡፡ የሚች የውርስ ሀብትም በፍርድ ቤት በመጣራት ላይ ያለ ስለሆነ የውርስ ድርሻ አልተለየም፡፡ በመሆኑም ንብረቱ ተሸጦ ለፍርዱ ገንዘብ ማስፈጸሚያ ሊውል አይገባም ብለዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የንብረቱ ስመ-ሀብት

ወደወራሾች ዞሯል፣ ካርታውም በስማቸው ይገኛል፤ ይሕም የውርስ ድርሻቸው መለየቱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ድርሻ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰጠቱ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ የውርስ ንብረት ያልተከፋፈለ የወራሾች የጋራ ንብረት ነው፡፡ ንብረቱ በአመልካች እና በሌሎች ወራሾች ስም መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ይሕ በሆነበት ሁኔታ የውርስ ሀብት ማጣራት ሂደት ይጠበቅ መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ አፈጻጸሙ ንብረቱ ላይ ሊቀጥል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የውርስ ሀብቱ በመጣራት ላይ ያለ ነው፡፡ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የውርስ ድርሻ አልተለየም፡፡ ስለሆነም የአፈጻጸም ክርክሩ የውርስ ማጣራት ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሊጠብቅ ይገባል የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የውርስ ድርሻው ተለይቶ ባልታወቀበትና አመልካች ይሕንን እየተቃወመ አፈጻጸሙ በንብረቱ ላይ መቀጠሉ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ንብረቱ ላይ የሚስትነትና የወራሽነት ማስረጃ ወጥቶ ስመ-ሀብቱ ተዛውሯል፡፡ የውርስ ማጣራት አቤቱታ ያቀረበ ሰው ካለ በራሱ የሚከራከር እንጂ አመልካች ሌሎች ሰዎችን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም፡፡ የፍርዱ ገንዘብ ብር 173,283.00 ነው፤ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የውርስ ድርሻ ከዚህ ገንዘብ በላይ ነው፡፡ በድርሻቸው ላይ አፈጻጸሙ መቀጠሉ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት ከያዘው ጭብጥና በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ከወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው እና ኤድሰን ካርጎ ኃ/የተ/የግል ማሕበር ጋር ተከራክረው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ ምክንያት ለፍርዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 1137 የሆነ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው ንብረት ነው በማለት ለእዳው መክፈያ እንዲሆን ጠይቀው አፈጻጸም ችሎቱ ንብረቱ እንዲከበር አድርጓል፡፡ አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ንብረቱ እንዲለቀቅ የተቃውሞ ማመልከቻ ያቀረቡት የተከበረው ንብረት የሚች ወንድይፍራው መንገሻና የእኔ ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት ነው፡፡ የሚች የውርስ ሀብትም በፍርድ ቤት በመጣራት ላይ ያለ ስለሆነ የውርስ ድርሻ አልተለየም፡፡ ስለሆነም በአፈጻጸም ሊከበር አይገባም የሚል ነው፡፡ ለፍርድ ማስፈጸሚያ የተከበረ ንብረት ላይ መብቱ ተነክቷል ያለ ሰው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት የተቃውሞ ማመልከቻ አቅርቦ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት በማሳየት ንብረቱ ከአፈጻጸም ውጭ እንዲሆን የመጠየቅ መብት አለው፡፡ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 3 ላይ አመልካች የሆነው ወገን ንብረቱ ላይ የተቀዳሚነት ሆነ የባለይዞታነት መብቱን የሚያረጋግጥለትን ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 419(1) መሠረት ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን እና ማስረጃውን መርምሮ ንብረቱ እንዲያዝ

ወይም እንዲከበር የሚያደርግ በቂ ምክንያት አለመኖሩን ሲረዳ የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የተቃውሞ ማመልከቻ ተከትሎ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የንብረቱ ስመ-ሀብት ወደወራሾች ዞሯል፣ ካርታውም በስማቸው ይገኛል፤ ይሕም የውርስ ድርሻቸው መለየቱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ድርሻ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰጠቱ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ ከክርክሩ የተገነዘብነው በአፈጻጸም የተከበረው ቤት ባለንብረት አመልካችና አቶ ወንድይፍራው መንገሻ ነበሩ፡፡ አቶ ወንድይፍራው መንገሻ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ሥመ-ሀብቱ በአመልካች ስምና በሚች ወራሾች ስም መዛወሩን የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካችም ንብረቱ በአመልካና በወራሾች ስም መዛወሩን ክደው አይከራከሩም፡፡ 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው የሚች ወራሽና ባለድርሻ መሆናቸውም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አፈጻጸም ችሎቱ በተለይም ሐምሌ 02 ቀን 2011 ዓ/ም በሠጠው ትዕዛዝ ዕዳው የሚፈጸመው የፍርድ ባለዕዳ በንብረቱ ባላቸው የውርስ ድርሻ ልክ ስለመሆኑ ገልጿል፡፡ ንብረቱ ወደ ወራሾች ሲዛወር በቤቱ ግማሽ ሀብት ላይ መብት ያላቸው ሰዎች የተለዩ በመሆኑ የውርስ ድርሻው ላይ አፈጻጸሙን ማስቀጠል የሚያስችል ነው፡፡ አመልካች በንብረቱ ላይ ያላቸው ግማሽ ድርሻ ለዕዳው መክፈያ እንዲውል ያልተደረገ በመሆኑ አፈጻጸም ሂደቱ መብታቸውን የነካ አይደለም፡፡ ሌሎች ወራሾች ውርስ ሀብት እንዲጣራ የጠየቁ ካሉና አፈጻጸሙ መብታቸውን የሚነካ ከሆነ መብታቸው የተነካባቸው ሰዎች በራሳቸው የተቃውሞ ማመልከቻ ሲያቀርቡ የሚመረመር ይሆናል፤ አመልካች ውክልና ሳይኖራቸው በራሳቸው ስም ስለሌሎች ሰዎች ሊከራከሩ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት አመልካች ያቀረቡትን የተቃውሞ ማመልከቻ ያልተቀበሉት የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትለው ስለሆነ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 253896 ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 267544 ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

2. አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ